# ለታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሆኑ ለማድረግ የወጣውን መመሪያ ለመሻር የወጣ መመሪያ ቁጥር 961/2015

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

   የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 129(1) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014 አንቀጽ 57 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ለታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 773/2013 እና 898/2014 ለመሻር የወጣ መመሪያ ቁጥር 961/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ስለመሻር**

   ለታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የወጣው መመሪያ ቁጥር 773/2013 እና የዚሁ መመሪያ ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 898/2014 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

4. **መመሪያው የሚፀናበት ቀን**

   ይህ መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር የድህረ ገጽ አድራሻ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት፣ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ
አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

UPLOADED ON 22 MARCH 2023